ጎቦ ዉቃው
መስከረም 2000

# ለ አንተ “የድህነት ፍልስፍና እና የፍልስፍና ድህነት” …ቅመም አይሆንም !

የዚህ ጽሁፈ መነሻ፤ የሞተው ጀግናዉ ወንድሜ ደም ባንተ በ ትንሹ በተደጋጋሚ ሲላገጠበት በ መስማቴ እና በማየቴ ነው… እንቶኔ ምንም ያህል ዕውቀትም፤ ችሎታም እንደሌለው፤ (የገደል ማሚቶነቱን) ፤እኔ እና እሱ በደምብ ስለምንተዋወቅ፤ ደካማነቱን ቢያንስ እንኩዋን ለኔ እንደማይክደኝ እርግጠኛ ነኝ። ነገር ግን ይህ የእለት እና የወር ገቢውን መሸፈኛውን የሚያገኝበት፤ የሆድ ግዴታው እንደሚያውተረትረው፤ አውቆትም ይሁን ሳያውቀው የተሰጠው የጥፋት ስልጠና ግድ ብሎት የሚያደርገው የመወራጨት አባዜ ሆነና ወዴት እንደሚረግጥም፤ እየረገጠም እንደሆነ አያውቀውም።

ከ አቅሙ እና ዕውቀቱ በላይ እንደሚያንጠራራውም ግልፅ ነው፤ ከዚህም በላይ ወራጅ ዉሃም ሆነ ፍሳሽ ለማሰተላላፍ እንደተጋደመ (ቧንቧ) ከመሆን በላይ ተግባር ስለሌው የእጀራዉን አባቶች የማስደሰት ሙከራው አልሞላ እያለው፡ከመስመር እያለፈበት ነው።

የ እሱ ዐይነቱ አጉራ ዘለልነት፤ አልገባውም ኢንጂ፤ ምክትል አለቆቹ እነኛ <u>“አዱ ገነት”</u> ላይ የተሰበሰቡት ከ አሥራ በላይ የማያልፉት <u>“የ ዐድዋ ወንበዴዎች”</u> እንኳን፤ መሰሪነቱን አንገታቸው ላይ፤ ከጫካም እንደ እንጀራ እናት ጡጦ ታሰሮላቸው ያደጉበት፤በደማቸው የገባውም፤ የ ግፍ ቁንጮዎቹም፤ የሚራመዱበት መንገድ መድረሻዉን (አደጋዉን) መገመት ሰለሚችሉ፤ ከብዙሃኑ ያገሬ ህዝብ የሚያጣላቸዉን፤ ሊያጣላቸው የሚችለዉን፤ጠንቅቀው ስለሚያወቁ፤ ያንተን ያህል አይዳፈሩም፤ ሲፈልጉ ባንተ እና ቢጤዎችህ ይጠቀሙአል <u>እንጂ፤በልጆቹ ደም ቢያላገጡ “አ ሁ ን ስ ባ ይ ኔ መ ጣ ህ !” እንደሚያሰኝ</u>፤የሚመጣዉን አደጋ ይገምቱአል፤ እንደተዳፈነ ዕሳት ቢቆሰቁሱት ሊነሳ የሚችለዉን ምድር አንቀጥቀጥ ሃይል ስለሚያወቁት፤ ከገቡበት ግንቦት 1983 ጀምሮ ጥንቃቄአቸው <u>“ልዩ ነው”</u>፤ ይህንንም እነሱ ቢቻ ሳይሆኑ አብረዋቸው አዱ-ገነት የዘለቁትም ሆዳቸዉ የከበዳቸዉ፤ “ተማርን ባዮቹ ታርጋቸዉ ፎረም 84” ተቢዬዎች የግዜ መግፊያ፤ ያዞ ዕንባ እ ንዳላዘልቃቸው ውዲያው ነው ያወቁት።

ከምስራቁ-ዓለም በተጨነ ጥይት፤ በቅጥረኛ ነፍሰ-ገዳዮች፤ አብዮት ጠባቂዎች ባደባባይ በግፈኛዉ ግራዚያኒ መንግሰቱ ጥይተ ለሞቱት ለ እነኚያ ለ እኔ ወንድሞች፤ እህቶች ጀግኖቹ ፤ወያኔም “የ ሰማዕታት ሀውለት ላቆም ነው!፤ ዐጥንታቸው ተለቅሞ ይዉጣ!፤ ብሎ የነበረው <u>“ያንድ ሰሞን የቴሌቪዥን ትርዒት“</u> ፤ የ ዓፄው ቤተ መንግስት መግቢያ “ሬድ-ካርፔት” አድርገውት የነበረው ተውኔት የቅርብ ግዜ ትዝታ ነው፤ ም ነ ው?! የሚለው የህዝብ ድምፅ ሲሰማ፤ ነገሩ ሲጣድ እና ሲፈላ፤ ለማርገቢያው <u>“የ መስረት- ድንጋይ ይጣል!”</u> ፤ <u>“የ ዲዛይን ውድድር ይደረግ!”</u>፤ ለ አደጋው ያላቸውን ፍራቻ ያሳይሃል፤ ዳሩማ ወያኔማ ወያኔ

ነው፤ ይህቺ ያድዋ ጮሌነትማ (ሊፕ-ሰርቪስ) መሆኑአን "ወጡ ሳይወጠወጥ.." እንደሆነ ጠንቅቀን እናዉቃለን፤ ከ እነኚያ ንፁሃን ዕልፍ ወጣቶች ደም ክብር በላይ፤ ለ አድዋዎቹ ወንበዴዎች ንግስና፤ ለ ኤርትራ ግንጠላ ባለዉለታዋ "አአ ህህ ያያ ! !" መታሰቢያ ቆሞ የለ፤ "እሱን ጢሲ ...." አለ የ አገሬ ኦሮሞ፤

በ እነኚህ የ አድዋ ወንበዴዎች የ ግፍ ዘመን፤ ገና ከ ጅምሩ በጠራራ ፀሐይ በራፉ ላይ ከ ተደፋው አሰፋ ማሩ እና በምርጫ 97 ማዕግስት ከምዕራቡ ዐለም በተጫነ ጥይት እና ስልጡን አነጣጥሮ ተኩአሽ ግንባሩን የተመታው ሙሽራው ያጎቴ ልጅ "ተስፋዬ"...፤ ሽብሬ ደሳለኝ...፤ የፈሰሰው ደማቸው አሁንም ትኩስ ነው፤ በጠቅላላው ቤተሰቡ ላይ ለደረሰው ሐዘን እና የህመሙ መጠን ከ እኛ በላይ የሚያምው የሚኖር አይምስለኝም።

በሚቹ በየጀግናው ኢሕአፓው ወንድሜ ምክኒያት በተለይ እናቴ እና በ አጋዚ ጦር በ ተገደለው ተስፋዬ ሞት የ አጎቴ ሚስት ከ ደንቡ በላይ ይኸው እስከ አሁን ማቅ እንደለበሰች፤ ምላው ወገንም በከባድ ሐዘን ላይ ነው። አነተ ግን ይኸው እስከ አሁንም ድረስ ከማንም ከሐዲ እና ጠላት በላይ ያልሞከሩትን ጭፍን ሙከራ እየሞከርክ በመሆኑ "ማሙሽ እሱ ኡፉ ነው!" እያልን ልንነግርህ ባልተገባ ነበር።

የዛሬዉ የኛ ልሳን ፤ የኛ ነፃ አዉጪ፤ በደርጉ ዘመንማ ምን ሆነህ? ምን እንደሰራህ? እንተዋወቅ የለ፤ ያሁነኛዉን ምድበህን (ሴል ሜምበርነትህ)፤ በ አድዋዎቹ ጮሌዎች ስልት፤ "ባገር ክደት ክስ ሽፋን ስም" የለበስከው ማሊያ አሰላለፍህን የደበቀልህ የሚመስልህ ደካማ ብትሆንም፤ በ እኔ ሚዛን ያንተ "ትንሽነት" (ቀላልነት)፤ ጉዳቱ ጊዜያዊ ነው የሚል ዕምነት ቢኖረኝም በዚያ ባንተ ትንሽነት መጠን (ልክ) የሚገኙትን ተላላ ወንድሞቼን ላንድ ቀን ግራ ማጋባት የለብህም የሚል ፅኑ እምነት አለኝ።

ዛሬ ግን እውቀት እንኩአን የለህም! "የዘሬ ያንዘርዝረኝ!" ሆነ እና ዋና ዋናዎቹ ደሞዝ ከፋዮችህ ያልደፈሩትን፤ እና ያላለፉትን መስመር በማለፍህ፤ አንተም ታውቀዋለህ፤ ይህ ድርጊትህ ፈንጠዚያዉ፤ ለ አድዋ ወንበዴዎች፤ ቅጥረኞቻቸው ሆዳሞች፤ ለባዶዎቹ አብዮት ጠባቂዎች፤ የ አብዮት ጠባቂ ልጆች፤ብቻ ናቸው እንደ "ትግሬ-ጀበና" የሚፈሉት፤ "ሰርጓ እንዳማረላት ሙሽራ" እነኚህም ካንገት በላይ ሊፈነድቁብን፤ ትከሻቸዉን ሊሰብቁብን አንፈቅድም፤ የ አንተም ሆነ የእነሱ "ፈንደቂያ" ከልብ ሳይሆን፤ በ አንተ ዙሪያ የሰበሰባቸዉም፤ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ እየኮረኮረ ዕረፍት፤ ጤና የነሳቸው፤የሰማዕታቱ፤የጀግኖቹ፤ የ ኢሕአፓ አባላቱ፤ የሙሽሮቹ ወንድሞቹ እህቶቹ ደም ነው ከትክክለኛ ፍትህ መደበቂያ ዳስ የጣልክላቸዉ መስሎአቸዉ ጮቤ የዳዳቸው፤ ይህንንም ከቶ አንፍቅድም።

የእኔ አይነቶቹ ዕልፍ ናቸው፤ በደርግ ጥይት መሃል መርካቶ በተገደለው በሙሺራው ወንድሜ ሞት እንዲሁም በ አጋዚ ጥይት መሀል ግንባሩን ተምቶ በሞተው በሙሽራው ያክስቴ ልጅ ደም ማላገጡን ቤተሰባቺን በሞላ ለደቂቃ በቀልድ አናየዉም ።

**አይ ድፍረትህ!** *ሌላው ከማሰገረምም የሚያስቀው የ ሰሞኑ ድራማህ፤ እንደ አምናው የ ምርጫ ሰሞን "ተግባር- ሊግ" ወጣቶች ያስገደልክበት ዕቃ ዕቃ ጫዋታ ሰሞኑን የሰባ- ሚሊዮን ሕዝብ ምርጫ እና ወደር የሌለዉን ጀግና የ ኢትዮጵያ ልጅ በ ኢንጅነር ሀይሉ ሻውል የ ዋሺንግተን-ዲሲ አቀባበል ስነ-ስርዐት ላይ፤ ሲሉ ሰምተህ የለ፤ እነኚሁኑ አብዮት ጠባቂዎችን እፍኝ ከማይሞሉ ልጆቻቸው ጋር በትንሽ ቡድን አደራጅተህ በ ገማ ዕንቁላል ለ ማስመታት መንጠራራትህ አጀብ ነው።*

**ተሰፍሮ የሚሰጠህ ምስህ ለምትቀባጥረው የሚመጠን አልመስል እያለህ የምታረገው መቅነዝነዝ "መ ስ መ ሩ ን አ ለ ፈ !" ለዲስኩርህ እና ለዱራ-ገፅህ መሙያ እራስህን ችለህ ለመቆም የ ዕውቀትና የሐቅ ድሕነት በ አቅምሕ ከ ምትሸከመው በላይ በመሆኑ (እዚያው ቀጣሪዎችህ ጋ ፤ ኮንትራቱን እንዲያቀሉልህ፤ የውሸትዋን "ያገር ክደት ክስ" እንዲያነሱልህ ተማጠን)።**

## ኤልያስ ላንተ "የድሕነት ፍልስፍና እና የ ፍልስፍና ድሕነት ኢሕአፓ ቅመም አይሆንም"

*ይህ መልዕክት ለ አንተ ብቻ ሳየሆን አባሪዎቺህ እና ቢጤዎቺህን ይመለከታል*